# ክፍል 3

# የገበያ ተኮር ግብርናና የምርት ዓይነት ብዛት ሂደትና ፖሊሲ

# Agricultural Commercialization and Diversification: Process and Policies

ማውጫ


1 መግቢያ ........ 1

2 ከእጅ ወደ አፍ (ህይወት ማቆያ) ምርት ወደ ገበያ መር ምርት ስርዓት ማምራት ........ 2

3 የምርት ምርጫ እስፔሻላይዜሽን በዳይቨርስፊኬሽን መካከል ........ 3

3.1 ከገበያ ከማይገዛ ወደ ከገበያ የሚገኝ ግብዓት መቀየር ........ 4
3.2 የኃይል ምንጭ ምርጫን መወሰን (እንስሳትና ሰው ወይንስ ሜካኒካል) ........ 5
3.3 የአፈር ለምነትን መጨመር (ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ወይንስ ፍግ/ ብስባሽ) ........ 5
3.4 የመኖ ገበያ እየጐላ መምጣት ........ 6
3.5 ስጋና ወተት ለሰው ምግብነት ........ 6

4 የገበያ ተኮርና ዳይቨርስፊኬሽን አሳሳቢነት ........ 7

4.1 የቤተሰብ ደህንነት ........ 7
4.2 የክልል ገቢ ክፍፍል ........ 7
4.3 የዋጋ አደጋና ዳይቨርስፊኬሽን ........ 8
4.4 የሃብት ቀጣይነት ........ 10

5 ለምርምርና ለፖሊሲ ያለው እንደምታ ........ 10

5.1 ምርምር ........ 10
5.2 የኢኮኖሚ ነጻነት ........ 11
5.3 የካፒታል ገበያ ........ 11
5.4 የንብረት መብት ........ 12
5.5 የውሃ መብት ዋስትና መኖር ........ 13
5.6 የገጠር መሠረተ ልማት ........ 13
5.7 የድጋፍ አገልግሎት ........ 14

6 ማጠቃለያ ........ 14

# 1 መግቢያ

የኢኮኖሚ እድገት፣ የከተሞች መስፋፋትና የሠራተኛ ጉልበት ከግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ እየወጣ መሄድ የግብርናውን ሥራ ገበያ ተኮር እንዲሆን አድርጉታል፡፡

ገበያ ተኮር ግብርና ማለት የግብርና ውጤትን ገበያ ከማውጣት ያለፈ ትርጉም አለው፡፡ ይሄውም የምርት ዓይነት ምርጫና የግብዓት አጠቃቀም ውሣኔ ትርፍን ከማሳደግ መርህ ጋር በእጅጉ የተያያዘ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በግብዓት በኩል በተለይ ስናየው ደግሞ ገበያ ተኮር የሚለው ጽንሰ ሃሳብ የሚገበዩና የማይገበዩ ግብዓቶችን በገበያ ላይ ሊኖራቸው ከሚችለው ዋጋ ጋር በማስተያየት ዋጋ እንዲኖራቸው ማድረግን ያሳያል፡፡ የግብርናው ስርዓት በገበያ እንዲመራ ማድረግ የግብርና ምርቶችን የበለጠ ገበያ መር ወደሆነ ሁኔታ መምራትን፣ ገበያ ላይ የማይውሉ ግብዓቶችን ገበያ ላይ በሚገኙ ግብዓቶች መተካትን፣ የተቀናጀ የግብርና ስራን በመቀነስ በአንድ የምርት ዓይነት ላይ ብቻ ማተኮርን የያዘ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በግለሰብ እርሻ ደረጃ ገበያ ማሳደግን የሚወስኑት የቤተሰብ የጉልበት ዋጋ ማደግና የምግብና ሌሎች የግብርና ምርቶች በገበያ ተፈላጊነት ማደግ ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 12፡- የግብርና ምርት ስርዓት ከገበያ ማደግ ጋር የሚያሳየው ፀባይ

| ገበያ ተኮር ደረጃው | የአርሶ አደሮች ዓላማ | የግብዓት ምንጭ | የምርት ስብጥር | የቤተሰብ ገቢ ምንጭ |
|---|---|---|---|---|
| ከእጅ ወደ አፍ (የሕይዎት ማቆያ) ምርት ስርዓት | በምግብ ራስን መቻል | ከቤት አካባቢ የሚገኙ | በጣም ሰፊ | በዋናነት ግብርና |
| ግማሽ ገበያ ምርት ስርዓት | ተጨማሪ ምርት ማምረት | ከገበያ የሚገኙና የማይገኙ | መጠነኛ የምርት ዓይነት | ግብርናና ግብርና ያልሆኑ |
| የገበያ ምርት ስርዓት | ትርፍን ማሳደግ | በአብዛኛው ከገበያ የሚገዙ | በአንድ ምርት ላይ ያተኮረ | በዋናነት ከግብርና ውጭ |

የቤተሰብ ጉልበት ዋጋ የሚጨምረው ከግብርና ውጭ ያለው የስራ እድል ሲያድግና ቤተሰቡ በዚህ ዕድል መጠቀም ሲጀምር ሲሆን የከተሞች መስፋፋት ደግሞ ዋጋውን የበለጠ ያንረዋል፡፡

ኢኮኖሚው እያደገ ሲሄድ ቀስ በቀስ ፍጹም ከእጅ ወደአፍ ከሆነና በበርካታ የምርት ዓይነቶች ላይ ከተመሰረተ ኑሮ በአንድ ዓይነት ምርት ላይ ወደአተኮረና ገበያ መር ወደ ሆኖ ምርት ስርዓት ይቀየራል፡፡ ከአንድ ዓይነት የምግብ ይዘት ወደ ተለያየ የምግብ ይዘት የመለወጡ ሁኔታ ለግብርና ምርት የቴክኖሎጂ ማደግ፣ የገጠር መሠረተ ልማት መሻሻል፣ ማለትም ወደ ስጋ፣ ፍራፍሬ፣ አትክልት ወዘተ. ሲያድግ ለአንድ ዓይነት የተለመደ የምግብ እህል የሚኖር ፍላጐት ይቀንሳል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚፈጠረው የቤተሰብ ገቢ ሲያድግና የሕዝብ ወደ ገበያ መፍለስ ሲጨምር ሲሆን የቤተሰብ ፍላጎት ልዩ ልዩ ንጥረ ነገር ይዘታቸው የተሟላ የምግብ ዓይነቶችን ወደ መፈለጉ ያዘነብላል፡፡

በመሠረቱ የምርት ዓይነት ብዛት (diversification) ማለት በነበረው የምርት ዓይነት ላይ ሌላ ዓይነት ምርት (ሰብል፣ እንስሳት፣ ወዘተ.) መጨመር ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጅ ገበያ ተኮር ደረጃ እየጨመረ ሲመጣ የተሰባጠረው የእርሻ ስርዓት ለአንድ ዓይነት የእርሻ ስርዓት በተለይ የገበያ ፍላጐትን ወደሚመልስ የምርት ዓይነት ቦታውን ይለቃል፡፡

የሩቅ ምስራቅ ኤሽያ ሃገሮች በገበያ ተኮር ግብርና ጐዳና እየተራመዱ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል የደቡብ ምስራቅ ኤሽያና ላቲን አሜሪካ ሃገሮችም ቢሆን ወደ ገበያ ተኮር ግብርና እየሄዱ ነው፡፡ በአጠቃላይ ዛሬ ከሃገር ሃገር ወይም ከክፍለ ዓለም ክፍለ ዓለም ፍጥነቱ ይለያይ እንጅ ሁሉም ሃገር ወደዚሁ ገበያ ተኮር ምርት ወደ ማምረት አቅጣጫ እያመራ ነው፡፡

# 2 ከእጅ ወደ አፍ (ህይወት ማቆያ) ምርት ወደ ገበያ መር ምርት ስርዓት ማምራት

የምግብ ምርት ማምረት ስርዓት ሕይወት ማቆያ፣ ከፊል ገበያና ገበያ መር ተብሎ ይከፈላል፡፡ ኢኮኖሚ እያደገ ሲሄድ ቤተሰቦች ከተለመደው በምግብ ራስን የመቻል ዓላማ ወደ ትርፍ ምርትና ገቢን የመጨመር ዓላማ ይሸጋገራሉ፡፡ እንዲሁም የቤተሰቡን ጉልበት ብቻ ከሚፈልግ የሕይወት ማቆያ ምርት ስርዓት የግዥ ጉልበት ወደ ሚፈልግና ለገበያ ወደ ሚያመርት የምርት ስርዓት እየተቀየረ ይመጣል፡፡

ሠንጠረዥ 13፦ በሩዝ ምርት አካባቢ የአመራረት ቅይጥ ለውጥ

| ገበያ ተኮር ደጃዎች | ዝቅተኛ ቦታ ሆኖ መስኖ ብቻ የሚጠቀም | ዝቅተኛ ቦታ ሆኖ በዝናብ የሚያመርት | በባህረ ሸሽ አካባቢ የሚያመርት | የከፍታ ቦታ ሩዝ የሚያመርት |
|---|---|---|---|---|
| የሕይወት ማቆያ ምርት ስርዓት | | • ሩዝ ብቻ<br>• እንስሳትና ዶሮ | • ሩዝ ብቻ<br>• ዝቅተኛ ዓሣ ምርት | • ሽፍቲንግ ካልቲቬሽን<br>• እንስሳትና ዶሮ |
| ከፊል ገበያ ምርት ስርዓት | • ሰፊ ሩዝ ምርት፣<br>• አትክልት<br>• መኖ ልማት | • ሁለት ጊዜ ሩዝ<br>• አነስተኛ የቤት እንስሳት | በበጋ ጊዜ የሚጠጣ ሩዝ | • አትክልት<br>• ስራስር<br>• በቆሎ |
| የገበያ ምርት ስርዓት | • ዓመቱን በሙሉ አትክልት<br>• ፍራፍሬ<br>• ሰፊ ዶሮና ዓሣማ እርባታ | ሰፊ ዶሮ እርባታ | ሰፊ ዓሣ እርባታ | • ሰፊ እንስሳት እርባታ<br>• ደን<br>• ከብት ርቢ |

ከላይ የሚታየው ሠንጠረዥ የሚያመለክተው የምርት ሥርዓቱ ከሕይዎት ማቆያ ምርት ሥርዓት ወደ ገበያ ምርት ስርዓት ሲሸጋገር በተለያዩ አካባቢዎች የምርት ዓይነት ለውጥ የሚኖር መሆኑንና ምርት ስርዓቱም በሁሉም አካባቢዎች በአብዛኛው በአንድ ዓይነት ምርት ላይ ብቻ የሚያተኩር መሆኑን ነው፡፡

# 3 የምርት ምርጫ እስፔሻላይዜሽን በዳይቨርስፊኬሽን መካከል

ገበያ ተኮር ምርት ለገበያ የሚመረተውን የምርት ዓይነት በብሔራዊ ደረጃ ከመጨመሩም ባሻገር በግለሰብ እርሻና በክልል ደረጃ ወደእስፔሻላይዜሽን እንዲተኮር ያደርጋል፡፡ ከላይ በሩዝ ምርት ላይ የተገለጸው ይህንን የሚአብራራ ነው፡፡ በተለይ በሰንጠረዥ 12 እንደሚታየው በከፊል ገበያ ምርት ስርዓት ውስጥ ከሚመረተው አብላጫው ለገበያ ነው የሚውለው፡፡ በተጨማሪም አብዛኛው ግብዓት ከገበያ የሚገኝ ነው፡፡

በሌላ በኩል በገበያ ላይ ያተኮረ የግብርና ስርዓት እየጨመረ ሲመጣ አንድ ሩዝ ብቻ የነበረው የምርት ስርዓት ወደተለያየና ለገበያ ወደሚመረቱ ዓይነቶች ይለወጣል፡፡ ከላይ እንደሚታየውም በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በዓሣ፣ በዶሮ፣ በአሳማ ላይ ያተኮረ ስራ ይሰራል፡፡ የከፍታ ቦታ ምርት ቢሆንም የቦታው ልዩ ሁኔታ እንደሚፈቅደው በእንስሳት ላይ ብቻ ትኩረት ወደ ማድረግ ያዘነብላል፡፡

ሰንጠረዥ 14፡- ከገበያ የማይገዙትን ግብዓቶች ከገበያ በሚገዙ መተካት

| ገበያ ተኮር ደረጃዎች | የእርሻ መሣሪያ | የአፈር ለምነት ግብዓት | መኖ | የሰው ምግብ |
|---|---|---|---|---|
| ሕይወት ማቆያ ምርት ስርዓት | • እንስሳት<br>• ሰው | የእርሻ ብስባሽ | የሰብል ተረፈ ምርት | በዋናነት በቤት ውስጥ የተመረተ |
| ከፊል ገበያ ምርት ስርዓት | ሞተር /እንስሳት፣ ሰው | • የእርሻ ብስባሽ<br>• ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ | የሰብል ተረፈ ምርት | በቤት ውስጥ የተመረተና ከገበያ የተገዛ |
| የገበያ ምርት ስርዓት | ሞተር | ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ | የተገዛ መኖ | በዋናነት የተገዛ |

የአግሮ ክላይሜት ችግርም በኢንቨስትመንት ሊታረም ይችላል። ይሄውም ለምሳሌ ሃበት በማፍሰስና ሰፊ የልማት ሥራ በመስራት ለሩዝ ሰብል ውሃን በመቆጣጠር በመስኖ ማጠጣት የሚቻል ሲሆን ለሌላው ብዙ ውሃ ለማይፈልግ ሰብል ደግሞ ትርፉን ውሃ በማፋሰስ የፍላጐትን ውጥረት ማርገብ ይቻላል። የከተሞች መስፋፋትና የንግድ ነፃነት ወደ ከፍተኛ የፍላጎት ውጥረት ስለሚመራ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውና ከምግብ ሰብል ውጭ ያሉ ሌሎች ሰብሎች እንደ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ስጋ፣ ዶሮ ያሉ ምርቶች እንዲመረቱ ያስገድዳል። ሌላው ቀርቶ የተቀናጀ ግብርና ይከተል የነበረ ስርዓትም በአንድ ምርት ላይ ወደ ማተኮር ስልት ያመራል። ምክንያቱም ገበያ የሚፈልገው አንዱን ብቻ ሊሆን ስለሚችልና ለዚያ ደግሞ የግድ የውጭ ግብዓትና አዲስ ቴክኖሎጂ ስለሚጠይቅ ሃብትን በአንድ ዓይነት ግን ደግሞ የገበያን ፍሰጎት ሊያረካ በሚችል ምርት ላይ ማዋል አስፈላጊ ስለሚሆን ነው።

## 3.1 ከገበያ ከማይገዛ ወደ ከገበያ የሚገኝ ግብዓት መቀየር

የቤተሰብ ጉልበት አማራጭ ዋጋ እየጨመረ መምጣት በተለይ ከግብርና ውጭ ያሉ የስራ እድሎች በማደጋቸው ምክንያት በአካባቢው ከተፈጥሮ ሃብት ይዘጋጅ የነበረውን ማዳበሪያ ለማዘጋጀት ጉልበት አይገኝም። ስለሆነም በአካባቢ ይመረት የነበረው የተፈጥሮ ግብዓት ከገበያ በሚገዙ እየተተካ ይሄዳል። በሕይወት ማቆያ ምርት ስርዓት ውስጥ ዋናው ግብዓት ከአካባቢ የሚገኝ ነገር

ነበር፡፡ ነገር ግን በገበያ ላይ ያተኮረ የምርት ስርዓት እያደገ ሲመጣ የግብዓትም ፍላጐት እየተለወጠ ይመጣና ከገበያ የሚገዙትን እንዲቀርቡ ያስገድዳል፡፡

### 3.2 የኃይል ምንጭ ምርጫን መወሰን (እንስሳትና ሰው ወይንስ ሜካኒካል)

አንጻራዊ በሆነ ሁኔታ የእርሻ ስራ ኃይል የሚጠይቁና ጥንቃቄ የሚሹ ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡ የማሣ ዝግጅት፣ ማጓጓዝ፣ መፍጨት፣ መከካትና መውቃት የመሳሰሉት ስራዎች ኃይል የሚፈልጉ ሲሆን አረም፣ ፍራፍሬ ለቀማ፣ ማበጠር፣ መንፋት የመሳሰሉት ደግሞ ጥንቃቄ የሚሹ ስራዎች ናቸው፡፡ ለእነዚህ ኃይል የሚጠይቁ ስራዎች የእንስሳት ኃይል የሚጠይቁ ሲሆን የሰው ጉልበት ደግሞ በጥንቃቄ መሰራት ላለባቸው ምርቶች ያስፈልጋል፡፡ የጉልበት ዋጋ ወይም ደሞዝ ሲጨምር ኃይል የሚጠይቁ ስራዎች ወደ ሞተር ይዞራሉ፡፡ ይሄ ደግሞ በሩቅ ምስራቅ ኤስያ ሃገሮች ታይቷል፡፡ እንስሳትን በሞተር የመተካቱ ዘዴ አትራፊ እንደሆነ እየታየ ነው፡፡ ይህ እውነታ ደካማ የገቢ እድገት ላላቸው ሃገሮችም ይሰራል፡፡ ነገር ግን እስከአሁን በድሃ አገሮች ውስጥ የእንስሳት ጉልበት እያገለገለ ያለው ማሽነሪ የማስገባት ሁኔታ ያለውን የሰው ጉልበት ሃብት ለመጠቀም አያስችልም በሚል ፖሊሲ የታሰረ ስለሚሆን ነው፡፡ ገበያ መር ምርት እየጨመረ ሲመጣ የሰው ጉልበትም በመሣሪያዎችና በኬሚካል እየተተካ ይሄዳል፡፡ እንደምሳሌ አረምና አጨዳ በአርም ማጥፊያ ኬሚካልና በማጨጃ ትራክተሮች እየተተኩ እንደሆነ መጥቀስ ይቻላል፡፡

### 3.3 የአፈር ለምነትን መጨመር (ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ወይንስ ፍግ/ ብስባሽ)

መሬትን ለምርት የመጠቀም ስራ መስፋፋት የሚችለው የአፈሩን ንጥረ ነገር በመተካትና ምርታማነትን ቀጣይ በማድረግ ነው፡፡ በሕይወት ማቆያ የምርት ስርዓት የአፈሩ ለምነት የሚተካው ከአካባቢ በሚገኝ ፍግ ወይም ብስባሽ ነው፡፡ ገበያ ተኮር ለሆነ የአመራረት ስርዓት ግን ምርትን ለመጨመር ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ካልታሰበ አይቻልም፡፡ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያን ተመራጭ የሚያደርግበት ምክንያት በመጀመሪያ የሚያስፈልገው ፍግ ወይም ብስባሽ መጠኑ በርካታ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፍግን ለማምረት በርካታ እንስሳት ስለሚያስፈልጉ ለእነዚህ የሚሆን መኖ ማግኘቱ ቀላል አይሆንም፡፡ ማጓጓዙም ቢሆን ከባድ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በዚህ ጉልበት ውድ በሆነበት ሰዓት እንደዚህ በብዛት የሚያስፈልጉ ነገር ግን ጠቃሚው ንጥረ ነገራቸው በጣም አነስተኛ የሆኑ ፍግን የመሰሉ ነገሮች መልሰው የሚሰጡት ትርፍ ትንሽ ነው፡፡ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያን ለመግዛት፣ ለማጓጓዝ፣ ለመጨመር የሚጠይቀው ዋጋ ከሚሰጠው ጠቀሜታ ጋር ሲነጻጸር ዋጋው አነስተኛ ነው፡፡ ከጠቀሜታው አንጻር ሲታይ ተመሳሳይ የንጥረ ነገር መጠን

ያላቸው ሰው ሰራሽ ማዳበሪያና ፍግ የሚሰጡት ምርት ተመሳሳይ ነው። ይህን ተመሳሳይ የንጥረ ነገር መጠን ለማምረት የሚያስፈልገው ፍግ ግን ከፍተኛ ነው። በእርግጥ ፍግ ከምርት መጨመር ሌላ የአፈሩን ይዘት በማሻሻል በኩል በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይነገራል። ይሁን እንጅ ይሄም ቢሆን በአሁኑ ሰዓት በሌላ ዘዴ እየተተካ ነው።

## 3.4 የመኖ ገበያ እየጐላ መምጣት

እንስሳትን ከሰብል ጋር አጣምሮ የማምረቱ ስራ ተፈላጊ የነበረው መኖ በቀላሉ ከአካባቢው ይገኝ ስለነበርና ተረፈ ምርትም  በግጦሽ ቦታ ላይ የነበረውን ጫና በቀላሉ መቀነስ በመቻሉ ነበር። ይሁን እንጅ በተለይ በአሁኑ ሰዓት የግጦሽ መሬት ለእርሻ እየዋለ በመሄዱ ከገበያ የሚገዛ መኖ መኖሩ ተመራጭ እየሆነ መጥቷል። ገበያ መር ምርት ላይ እንስሳትን አስሮ የገበያ መኖ መቀለቡ ተመራጭ ሆኗል። ሐን የተባለ ሰው (1992) የውጭ ኢንዱስትሪ በኤስያ ሃገሮች እያደገ መምጣቱን በመግለጽ በ1990ዎቹ በአጠቃላይ 101 ሚሊዮን ቶን ውህድ መኖ በኤስያ ፓስፊክ ክልል የተመረተ ሲሆን በተለይ ቻይናና ጃፓን ከፍተኛ አምራቾች እንደነበሩ ያብራራል። ከዚህ ውስጥ ቻይና 39 ሚሊዮኑን፣ ጃፓን ደግሞ 29 ሚሊዮኑን ቶን ያመረቱ መሆኑን ገልጿል። የገበያ መኖ በተለይ ለዶሮ፣ ለዓሣማ፣ ለቀንድ ከብት እርባታ ተፈላጊነቱ እየጨመረ ነው። ስለሆነም የእንስሳት ምርት ገበያው እየጨመረ ከመምጣቱና የቆየው የመኖ አሰባሰብ ዘዴ ከሚጠይቀው ጉልበትና ትራንስፖርት አንጻር ሲታይ የገበያ መኖው ተመራጭ ሆኗል።

## 3.5 ስጋና ወተት ለሰው ምግብነት

የኢኮኖሚ እድገት፣ የቤተሰብ ጉልበት አማራጭ ዋጋ ማግኘቱና ለገበያ የተመረተ ወተትና ስጋ በብዛት መገኘት በሕይወት ማቆያ ምርት ስርዓት የተመረተውን ኢኮኖሚአዊ አያደርገውም። የገጠሩ ህብረተሰብም ከመንገድ ርቆ የራሱን የምግብ ፍጆታ ብቻ በማምረት የሚኖርበት ሁኔታ እየተለወጠ ይሄዳል። የመንገዶች መገንባትና የገበያ መሠረተ ልማቶች መስፋፋት ከመገናኛ እጅግ በጣም ራቅ ላሉ አካባቢዎች ካልሆነ በስተቀር የህይዎት ማቆያ ምርት ስርዓቱ ዕድሜ እያጠረና ቀጣይነቱ እየቀረ ይሄዳል። በገጠር የሚኖር ህብረተሰብ ኑሮ ሲሻሻልና የመገናኛ መንገዶች መኖር  እንደ ሥጋ ያሉ ምርቶች በቀላሉ በየአካባቢው እንዲደርሱ ስለሚያደርግና የህብረተሰቡም የመግዛት አቅም ስለሚያድግ ሰዎች ወተትና ስጋን በበዓል ቀን ብቻ ከመመገብ አልፈው የዘወትር ምግብ ማድረግ ይጀምራሉ።

# 4 የገበያ ተኮርና ዳይቨርስፊኬሽን አሳሳቢነት

የእርሻ ምርት በገበያ ተኮር ምርትና በዳይቨርስፊኬሽን ሂደት መለወጥ ብዙ አሳሳቢ ነገሮችን አስነስቷል፡፡ እነዚህም አሳሳቢ ነገሮች የቤተሰብ ደህንነት፣ የክልል ገቢ ክፍፍል፣ የገበያ አደጋና የሃብት ቀጣይነት ናቸው፡፡

## የቤተሰብ ደህንነት

ቮን ብራውን (1995) እንዳጠናው ከውጭ የሚገኙ ግብዓቶችን አነስተኛ በሆነ ሁኔታ የሚጠቀሙና የሕይወት ማቆያ ምርት ስርዓት የሚከተሉ አካባቢዎች ከገበያ በብዛት ግብዓት ገዝተው ሰፊ ምርት ለገበያ ወደማምረት ሂደት ሲለወጡ ድሃዎች የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ምክንያቱም በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የጉልበት ዋጋ ውድ ይሆናል፡፡ በዚህም ገበያ ተኮር ምርት ስርዓት የስራ እድልን በመፍጠር ጥሩ አስተዋጽኦ ያለው ሲሆን የንግድ ምርቱን በባለቤትነት የሚያመርቱትም ሆኑ ተቀጥረው የሚሰሩት በቀጥታ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡ ይህ ጠቀሜታ የህጻናትን የምግብ ሁኔታ ከማሻሻል ጋርም ይያያዛል፡፡ ምክንያቱም ገበያ መር ምርት ስርዓት የቤተሰብ ገቢን ስለሚጨምር ለህፃናት ዕድገት አስፈላጊ የሆኑትን አልሚ ምግቦች የመመገብ አቅም ይጨምራል፡፡

ይሁን እንጅ አሁንም ይሄ ቮን ብራውን የተባለ ሰው (1995) እንዳጠናው ገበያ ተኮር ምርት ስርዓት አንዳንድ ጊዜ የቤተሰብ ደህንነት ሊጐዳ የሚችልበትን ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡ ይህም ውድቀት የሚከሰተው በተለይ የተቋማት፣ የፖሊሲ ወይም የገበያ ውድቀት ሲኖር ነው፡፡ ስለሆነም የመንግስት ፖሊሲ ከህይወት ማቆያ ወደ ንግድ ተኮር ምርት ስርዓት ሲለወጥ ድሃዎችን በማይጐዳ መልክ እንዲሆን የማመቻቸት ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ወደ አዲሱ የምርት ስርዓት የሚደረገው ለውጥ ድሃዎችን በጣም የሚጐዳ ይሆናል፡፡

## የክልል ገቢ ክፍፍል

አንዳንድ ጊዜ ገበያ ተኮር ምርት ባካሄዱና ባላካሄዱ አካባቢዎች፣ ክልሎች መካከል ልዩነቱ ሊባባስ ይችላል፡፡ ይሄውም ገበያ ተኮር ምርት ስርዓት ከሚከተሉ አካባቢዎች በሚመረተው የተትረፈረፈ ምርት ምክንያት ገበያ ተኮር ምርት ስርዓትን የማይከተሉ አካባቢዎች በዋጋ መውደቅ ችግር ሊመቱ ይችላሉ፡፡ ይህ ሁነታ በሁለቱ አካባቢዎች መካከል ያለውን ህይወት በጣም የተራራቀና የተለያየ ደርገዋል፡፡ ይሁን እንጅ ገበያ ተኮር ምርት በሚያመርቱ አካባቢዎች ውስጥ በሚፈጠረው የጉልበት ጥያቄ በደካማ አካባቢዎች የሚኖረውን ትርፍ ጉልበት ይወስደዋል፡፡ በዚህም ገቢ ከገበያ ተኮር አካባቢዎች ወደ ሌሎችም የመከፈል እድል ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ምርት

በትርፍ ከተመረተበት እጥረት ወዳለበት በቀላሉ ይጓጓዛል፡፡ ስለሆነም የሕይወት ማቆያ ምርት የሚያመርቱ አካባቢዎች በተዘዋዋሪ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡ በተለያዩ ክልሎች መካከል የሚኖረው የገቢ ልዩነት ሊጠብ የሚችለው በትክክል የሚሠራ የገበያ ስርዓት ሲኖር ነው፡፡ የተስተካከለ የገበያ ስርዓት ከሌለ ግን ልዩነቱ እንዳለ ይቀጥላል፡፡ ብሎም በጣም እየተበላሸ ይሄዳል፡፡ በእርግጥ ደልጋዶ (1995) የተባለ ሰው እንደሚያነሳው ሃሣብ በአፍሪካ ውስጥ በአካባቢዎችና በሴክተሮች መካከል ባለ ጥብቅ የገበያ ቁጥጥር ስርዓት ምክንያት ገበያ ተኮር ምርት ስርዓት በሚፈለገው ፍጥነት ሊያድግና ሊስፋፋ አልቻለም፡፡ በኤስያ ግን ክፍት የኢኮኖሚ ስርዓት ስላለ ከገበያ ተኮር ምርት ሂደት ተጠቃሚዎች ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩል በአፍሪካ በትራንስፖርትና በሌላም ከገበያ ጋር የተያያዙ ነገሮች መወደድ ኢኮኖሚውን በመጠኑም ቢሆን ዝግ አድርጎታል፡፡ ስለሆነም የአፍሪካ የኤክስፖርት ዋጋ ውድ ነው፡፡ ከፍተኛ የገበያ ዋጋ ደካማ መሠረተ ልማት፣ የረዥም እርቀትና የአነስተኛ ምርት ነጋዴዎችን በቀጥታ የመቆጣጠር ፖሊሲና የማጓጓዣ መኪናዎችን መለዋወጫ መቅረጥ ውጤት ነው፡፡ በከፊል የግልጽነት ተፈጥሮ ያለው የአፍሪካ ኢኮኖሚ ለገበያ የማይውሉ የምግብ ሰብሎችን የምርታማነት እድገት ስለማያበረታታ ገበያ መር የኤክስፖርት ሴክተር ገና ከጅምሩ እንዲወድቅ አንቆ በመያዝ ይታወቃል፡፡ ይህም ማለት ለምግብ ፍጆታ የሚሆነው ምርት ተፈላጊነቱ ስለሚያድግ ዋጋው ወደ ገበያ ከሚውለው የበለጠ ይሆንና ወደ ውጭ ገበያ ከማቅረብ ሃገር ውስጥ መሸጡ ተመራጭ ይሆናል ማለት ነው፡፡ የምግብ ዋጋ መናር ማለት በግብርና ስራ የተሰማራው ሠራተኛ በፍተኛ የኑሮ ውድነት እንዲጠቃ ያደርጋል፡፡ የዚህ ሁኔታ መፈጠር ለውጭ ገበያ የሚውሉ የእርሻ ምርቶች ጉልበት ዋጋን ስለሚያንረው አርሶ አደሩ ለውጭ ገበያ የሚሆኑ ሰብሎችን ለማምረት አይበረታታም፡፡ በዚህ የተጠላለፈ የምርትና የገበያ ሁኔታ ምክንያት ኋላ ቀር ተቋማትና አካባቢዎች ሌሎቹ ወደ ገበያ ስርዓት ውስጥ ገብተው እንዳያድጉ ወደኋላ ጎታች ይሆኑባቸዋል፡፡ በዚህ የተነሳ ደልጋዶ (1995) እንደሚለው መንግስት አካባቢና ሰብል ተኮር ፖሊሲ ቢከተል ለገበያ መር ምርት ስርዓትና ለዳይቨርስፊኬሽን ማበረታቻ ለመስጠት የሚያስችል ቁልፍ ሚና ለመጫወት ያስችለዋል፡፡

*የዋጋ አደጋና ዳይቨርስፊኬሽን*

በግብይት ላይ ያለውን የመጠን ቁጥጥር በማንሳትና የውስጥ ንግድ እድልን በመክፈት የሃገር ውስጥ ገበያን ነጻ ማድረግ የገበያ መር ምርትን ለማፋጠን ቁልፉ እርምጃ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የውስጥ ገበያን መክፈት በዓለም አቀፍ ዋጋ ተለዋዋጭነት ምክንያት አምራቾችን ለአደጋ ያጋልጣል፡፡ መንግስታት በሃገር ውስጥ ገበያ ጣልቃ በመግባት የዋጋ ማረጋጋት ስራ ይሰራሉ፡፡ በጥቂት የግብርና ምርቶች ኤክስፖርት ላይ ብቻ ማተኮር ለዓለም አቀፍ ዋጋ አደጋ እንደሚጋለጥ እየታየ ነው፡፡ የውጭ ምንዛሪ በሚያስገኙ ጥቂት

ምርቶች ላይ አፍሪካውያን ስለሚያተኩሩ በእነዚ ምርቶች ላይ ከዓመት ዓመት ያለው የዋጋ መዋዠቅ አለመረጋጋትን ፈጥሯል። ከሰሐራ በታች ባሉ ሃገሮች በ1970 እና በ1994 እ.ኤ.አ በጥቂቱ ወደውጭ በሚላኩ ምርቶች ላይ የዋጋ መቀነስ ተከስቷል። ስለሆነም ይህ ከላይ የተነሳውን ሁኔታ ለመለወጥና አደጋውን ለማስቀረት አፍሪካ ወደውጭ የምትልከውን ምርቷን በዓይነት ማሳደግ እንዳለባት ምሁራን ይስማማሉ። ከንግድና ከማክሮ ኢኮኖሚ ጋር በተያያዘ የዳይቨርስፊኬሽንና ዋጋ አደጋ ዝምድና የሀገር ውስጥና የውጭ ዋጋን ለማስተሳሰር በጣም ወሳኝ ነው። ዳይቨርስፊኬሽን በአምራቹ ደህንነት ላይ የሚደርስን አደጋ ለመቀነስ ትክክለኛ መፍትሄ እንደሆነ ይታያል። ከላይ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ ኩይሮዝና ቫልደስ (1995) እንደጠቀሱት እታች በቤተሰብ ደረጃ የዳይቨርስፊኬሽን መኖር የዋጋን አደጋ በሚፈለገው ደረጃ ላይቀንሰው ይችላል የሚል አባባል አላቸው። ምክንያቱም ለገበያም ይሁኑ ለምግብ የሚመረቱ የግብርና ምርቶች ዋጋ በእጅጉ የተየያዙና ለአለም አቀፍ ሰብል ምርት ዋጋና ለላዕላይ ኢኮኖሚ መዋዠቅ ተመሳሳይ ምላሽ ስለሚሰጡ ነው። ስለሆነም በቤተሰብ ደረጃ የሰብልን ምርት ዳይቨርሲፋይ ማድረግ ብዙም የዋጋን አደጋ አይቀንስም። በተጨማሪም የዳይቨርስፊኬሽን ሂደት የተለያዩ ሰብሎችን ዋጋ በአንድነት ሊጨምረው የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ምክንያቱም በበላተኛው በኩል ስናይ የአመጋገብ ስርዓት ተሻሻለ ማለት ሰዎች የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን በቀን ተቀን ምግባቸው ላይ ማስገባትን ስለሚያዘወትሩና ለተለያዩ ሰብሎች ያላቸው ፍላጎት ስለሚጨምር ዳይቨርሲፋይ ተደርገው የተመረቱት ሰብሎች ዋጋ በአንድነት ይጨምራል። በሌላ በኩል ደግሞ የአቅርቦቱን ሁኔታ ስናይ የገበያዎች መስፋፋትና የመሰረተ ልማት መሻሻል የተለያዩ የምግብ አይነቶች ከየአካባቢው እንዲቀርቡ የተመቸ ሁኔታ ስለሚፈጥርና ለበላተኛው በዓይነት ስለሚያቀርብለት አሁንም የተለያዩ ሰብሎች ዋጋ በአንድነት ሊያድግ የሚችልበት ሁኔታ ይፈጠራል ማለት ነው። ከላይ የተጠቀሱት አጥኚዎች እንደሚሉት በቤተሰብ ደረጃ የዳይቨርስፊኬሽን መኖር በራስ እንደመውደቅ ነው ይላሉ ምክንያቱም እያንዳንዱ ምርት ዳይቨርሲፋይ በሆነ ቁጥር የሁሉም ምርቶች ዋጋ በአንድ ላይ የማደግ ዕድል ይኖራል። ስለሆነም ዳይቨርሲፋይ በማድረጋቸው የተለየ የዋጋ ጭማሪ አይኖራቸውም ማለት ነው። ይሁን እንጂ ከኤኮኖሚ እይታ አንፃር ሲታይ የተለያዩ ምርቶች በጋራ ከፍተኛ ዋጋ መኖር ማለት ከፍተኛ ችግር መኖሩን አያመለክትም እንዲያውም ኤኮኖሚው ያንዣበበበትን አደጋ ይቀንስለታል። እንደ ኩይሮዝና ቫልደስ (1995) እንደገለጹት የገበያ ሰብሎችን ወደ ውጭ የሚልክና የምግብ ሰብሎችን ከውጭ የሚያመጣ ኤኮኖሚ በሁለቱ ሰብሎች ላይ በሚታየው ተመሳሳይ የዋጋ መጨመር ወይም መቀነስ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል። አምራቾችም ቢሆኑ ወደ ውጭ በሚላኩ የገበያ ሰብሎችና ከውጭ በሚገቡ የምግብ ሰብሎች ተመሳሳይ የዋጋ አቅጣጫ መኖር ሊጠቀሙ ይችላሉ ምክንያቱም በተለይ ከውጭ የሚገባውም ሆነ ወደ ውጭ የሚወጣው ሰብል ዋጋ ከቀነሰ የሃገር ውስጥ አምራቾች ላመረቱት ምርት ትክክለኛ ዋጋ የማግኘት

ዕድሉ ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ባይሆን የሁለቱ የምርት ዓይነቶች ዋጋ አንድ አቅጣጫ በማይዝበት ጊዜ የሚደርስባቸውን የዋጋ ጉዳት ያህል አያገኛቸውም፡፡ በአጠቃላይ የንግድ ማስተካከል እርምጃ ውጤቱ ዳይቨርስፊኬሽንን በእያንዳንዱ አምራች ደረጃ ሳይሆን በሃገር ኤኮኖሚ ደረጃ መሆኑን ያመላከተ ሊሆን ይገባዋል፡፡

### የሃብት ቀጣይነት

የእርሻ ስራን በዘመናዊ መንገድ የማስፋፋቱ ተግባር ብዙ ጊዜ ከአካባቢ የሚገኙ ግብአቶችን ከገበያ በሚገኙ ግብዓቶች የመተካቱን ተግባር ያጠቃልላል፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ረገድ የነፍሳት ተባይና የአረም ማጥፊያ የመሳሰሉትን መጠቀም በአካባቢና ብሎም በጤና ላይ አደጋ ያስከትላሉ፡፡ በተለይ እነዚህ ኬሚካሎች መርዛቸውን እንደያዙ የመቆየት እድላቸው ሰፊ ስለሚሆን በጤና ረገድ ከፍተኛ ወጪ ያስከትላሉ ፡፡ ይህን አደጋ ለመቀነስ የእነዚህን ኬሚካሎች ታክስ መጨመርና የተሰጣቸውን ድጐማ ማንሳቱ አጠቃቀማቸውን ለማስተካከል ያመቻል፡፡ ምክንያቱም አምራቹ የተለያየ አማራጭ ቴክኖሎጂ ማለትም እንደ የተቀናጀ የተባይ መከላከል የመሳሰለ የተባይ ጥቃትን የሚቀንስ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀም ያደርገዋል፡፡

በሌላ በኩል ዳይቨርስፊኬሽን መጠቀሙ የተባይ ክስተትን ይቀንሰዋል፡፡ በተለይ አንድ አይነት ሰብል ብቻ ሲጠቀሙ የነበሩ አካባቢዎች የሰብልን ዓይነት ሲያበዛ፣ ከዓመት ዓመት ሲያቀያይር ተባዮች ክስተታቸውን ይቀንሳሉ፡፡

## 5 ለምርምርና ለፖሊሲ ያለው እንደምታ

ከረጅም ጊዜ ስትራቴጂ አንፃር ገበያ መር ምርትንና በኢኮኖሚ ደረጃ ዳይቨርስፊኬሽንን ለማፋጠን የሚታዩ ቁልፍ መሠረታዊ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ምርምር

የምርምር ቀዳሚ ዓላማው በገበያ መር ምርት ስርዓትና በዳይቨርስፊኬሽን ሂደት ውስጥ ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ቴክኖሎጂዎችን ማመንጨት ነው፡፡ ለዳይቨርስፊኬሽን ምላሽ ለመስጠት ብቻ ምርምር ከአንዱ የሰብል ዓይነት ወደ ሌላ የሰብል ዓይነት በፍጥነት መዛወር የለበትም፡፡ ምርትን መጨመር ከሚለው ዓላማ በተጨማሪ ምርምር ለአርሶ አደሮች የተሻለ የሰብል አማራጭ

እንዲኖራቸው ማድረግም ተገቢ ነው፡፡ የሕዝብ ብዛትንና ለምግብ ሰብል ያለውን ጥያቄ ለመመለስ ሲባል ምርምር የዋና ዋና የምግብ ሰብሎችን ምርታማነት የመጨመር ፍላጐት ይኖራል፡፡

ምንም እንኳ የምርምር ተግባር አርሶ አደሮችን የሰብል ምርጫ እንዲኖራቸው ቢያግዝም ቅድሚያ ትኩረቱ በየትኞቹ ሰብሎች ላይ መሆን እንዳለበት በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል፡፡ ስለሆነም የሰብል ምርጫ መኖር አይቀርም ማለት ነው፡፡ ደልጋዶ (1995) እንደጠቀሰው ምርታማነትን ለመጨመር ለምርምርና ኤክስቴንሽን መንግስት ኢንቨስት አደረገ ማለት የግድ ብሎ ወደ ተወሰኑ ሰብሎች (commodity) ያደላል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም እንደ አፍሪካ ባሉና የተለያየ የእርሻ ሥነ-ምህዳር ያላቸው ቦታዎች በኮሞዲቲ ማተኮር ማለት አካባቢዎችን፣ ማህበረሰቦችን፣ ወዘተ. በማየት የሚሰራ ሲሆን በዚህ የተነሳ የሚያተኩርባቸው ሰብሎች በርካታ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

### የኢኮኖሚ ነጻነት

ሄዶ ሄዶ የዳይቨርስፊኬሽን ሂደት በዓለም ዋጋ ዘንድ ከሚንፀባረቁት ሸቀጦች፣ ተዛማጅ ዋጋና ውድ ከሆኑ ሃብቶች ጋር የተሳሰረ መሆን አለበት፡፡ በሃገር ውስጥና በውጭ ያለው የዋጋ የረጅም ጊዜ ልዩነት ለኢኮኖሚው ውድ ይሆንበታል ፡፡ የሃገር ውስጥ የሸቀጦች ዋጋ ከዓለም ዋጋ ዝቅ ካለ አርሶ አደሮች ይቀጣሉ፣ ማበረታቻም ይቀንስባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሃገር ውስጥ ዋጋ ከዓለም ምርት ዋጋ ከበለጠ ሸማቹ ይጎዳል፣ የማምረቻ ሃብቶች ሁሉ የበለጠ ሸቀጥ ለማምረት ይውላሉ፡፡

የኢኮኖሚ ነጻነት ዋና ዋና ይዘቶች የሚባሉ የንግድ ክልከላን ማለትም በመጠን ላይ የሚደረግ ጫናንና ወደ ውስጥ በሚገቡት ላይ ታሪፋ መቀነስን፣ የማክሮ ፖሊሲዎችን ማስተሳሰር፡፡ ይህም ማለት የሸቀጥ እጥረትን መቀነስ፣ የልውውጥን ቁጥጥር ማርገብ፣ በአጠቃላይ የገበያ ነጻነት እንዲኖር ማድረግ ማለት የፋይናንስ ገበያ ነጻነት፣ የፀጋዎች ነጻነት ማለት ነው (ኩይሮዝ እና ቫልዴስ 1995)፡፡ የዚህ ለውጥ ሂደት የዓለም አቀፍ ንግድ እድልን ይከፍታል፡፡ ለአምራቾች ውሣኔ የዋጋ ምልክት ይሰጣል፣ በአጠቃላይም የኢኮኖሚ ዳይቨርስፊኬሽንን ያበረታታል፡፡

### የካፒታል ገበያ

የገበያ ነጻነት እድል በጨመረ ቁጥር አደጋም ይጨምራል፡፡ የሃገር ውስጥ ምርት ዋጋ ከዓለም አቀፍ ዋጋ ጋር በጣም በተጠጋጋ ቁጥር ለግብርና አምራቾች የዋጋ መዋዠቅ ይገጥማቸዋል፡፡ በገጠር ቤተሰብ በኩል የአደጋን መስፋፋት ለመቀነስ የገንዘብ ቅንጅት ያስፈልጋል፡፡ በገበያ መር የግብርና ምርት አማካይነት ገቢ የመጨመር አቅም በሰፊው ለመጠቀም፣ ጠቃሚ ምርታማ

ሃብቶችን ለመገንባትና የሰው ሃብትን የተሻለ ለማድረግ የገንዘብ ገበያው በቤተሰብ ውስጥ መካተት አለበት፡፡ የገጠር የገንዘብ ስርዓት በፍጥነት በታችኛው የህብረተሰብ ክፍል አካባቢ ማደግ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይ ገበያ መር ግብርና ወደ ከፍተኛ ክፍያ ስለሚያመራ ገበያ መር ሂደት በራሱ ውጤታማ፣ ድጐማ የማይጠይቅ የገጠር ባንክ በዝቅተኛ ወጭ የሚያስተናግድ እንዲኖር ያበረታታል፡፡ ፍቱን የገጠር የገንዘብ ተቋም የገበያ መር ጥቅም በህብረተሰቡና በአጠቃላይ በክልሉ ውስጥ እንዲስፋፋ ያግዛል፡፡

*የንብረት መብት*

አጠቃላይ የኢኮኖሚ ነጻነት የኢኮኖሚ ዳይቨርስፊኬሽንና የገበያ መር ምርት እድል መስጠት አንዱ በህሪው ነው፡፡ በተጨማሪም የውሃ፣ መሬትና ሌሎች ሃብቶች ላይ ለሚኖረው የአረሶ አደሮች መብት አያያዝና  አጠቃቀም ከፍተኛ ግምት ያስቀምጣል፡፡ የመሠረታዊ ሃብቶች ማለትም እንደ መሬት፣ ውሃ ያሉት መብቶች በሚገባ ካልተተረጎሙና በሥራ ላይ ካልዋሉ በእነዚህ ሃብቶች በአግባቡ የመጠቀሙ ሁኔታ ዝግ ይሆናል፡፡ በገበያ መር ምርት ስርዓት ላይ የሚከሰት ውድቀት ከሂደቱ ጋር በተያያዘ ሳይሆን በእነዚህ የተፈጥሮ ሃብቶች ላይ ያለ መብት በአግባቡና በግልጽ ባለመታወቁ ነው፡፡ በተለይ በገበያ መር ምርት ስርዓት ማደግና ለተፈናቀሉ ባለመሬቶች በሚከፈለው ድጐማ ማደግ ምክንያት የመሬት የተጣራ ገቢ ሲጨምር የመሬት የመጠቀም መብት ችግር ይባባሳል፡፡ ስለሆነም የመሬት መብትን በከፍተኛ ደረጃ ማስጠበቅ ገበያ መር ምርት ሁኔታን ያሻሽላል፡፡

የተሻለ የመሬት ገበያና የሃብት ዋስትና መብት ለግብርናው ማደግና ለውጤታማነት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ (ፊደርና ሌሎች 1988፣ ቢንስዋንገርና ሌሎች 1993)፡፡ የመሬት ዋስትና መብት ለአርሶ አደሮች በመሬታቸው ላይ የበለጠ ዋጋ አውጥቶ ለማሻሻልና ለረጅም ጊዜ ምርታማ መሆን በጣም አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ገበያ መር የእርሻ ስርዓት ለመከተል ይገፋፋል፡ የካፒታል ገበያን በማቀናጀትና ነጻ በማድረግ በኩል የመሬት ዋስትና መብት ከገበያ መር እርሻ ስርዓት ጋር ይተሳሰራል፡፡ ምክንያቱም የዋስትና መብት አርሶ አደሮች ረጅም ጊዜ ከኢንቨስትመንት ጥቅም የማግኘታቸውን ሁኔታ ስለሚጨምርና ፍላጐታቸውንም ስለሚያሳድግ ወደ ገበያ መር ስርዓት እንዲያተኩሩ ያነሳሳቸዋል፡፡ ለግብዓት መግዣና መሬትን ለማሻሻል ለሚፈለግ ወጭ አበዳሪዎች ፈቃደኛ እንዲሆኑና ለብድርም ማስያዣ ለመሆን እንዲችል የመሬት የዋስትና መብት እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ከላይ የገለጽናቸው ፀሃፊዎች ይገልጻሉ፡፡

ውሃ የመጠቀም መብትንም ማረጋገጥ አርሶ አደሩ የሰብል ምርት ስርዓቱን ዳይቨርስፋይ እንዲያደርግ ያግዘዋል፡፡ በዕርግጥ በርካታ ባለሙያዎች እንደሚስማሙበት በአግባቡ ባልተያዘ የመስኖ አውታርና እንደሁኔታው በማይለዋወጥ የውሃ አጠቃቀም ስርዓት ምክንያት ዳይቨርስፊኬሽን በመስኖዎች አካባቢ ችግር ገጥሞታል /ዓለም ባንክ 1988/፡፡ በዚህ የተነሳ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ መፍትሄ እየተጠየቀ ነው፡፡ በተለይም የመስኖ ውሃ በቦይ መልቀቅን፣ ትርፍ ውሃ ማፋሰስን የሚያሻሽል ኢንቨስትመንት መኖር ሊከሰት የሚችለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ለመፍታት ጠቃሚነቱ እጅግ አስፈላጊ እየሆነ ነው፡፡ በመስኖ አውታር አካባቢ ላለው ውድቀት እንደ ሮስግራንትና ሌሎች 1995 አባባል ዋናው ምክንያት በመሠረታዊነት ማዕከላዊ በሆነ ሁኔታ ከሚታደል የነጻ ውሃ የተነሳ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የውሃ ሃብትን ያላግባብ እንዲጠቀሙበት ክፍተት ይፈጥራል፡፡ ነገር ግን በዋጋ የሚቀርብ የመስኖ ውሃ አርሶ አደሮች አነስተኛ የውሃ መጠን የሚፈልጉ ሰብሎችን እንዲመርጡ ያደርጋል፡፡

### የውሃ መብት ዋስትና መኖር

- የውሃ መብት ዋስትና መኖር ከመሬት ዋስትና መብት ጋር የተመሳሰለ ጠቀሜታ አለ፡፡ ይሄውም ለረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት መኖርና ለገበያ መር ምርት ስርዓት መዳበር ያግዛል፡፡
- ለማንኛውም የውሃ እንደገና ስርጭት፣ ለውሃ ወደሌላ ዝውውር ካሣ ስምምነታቸውን በመጠየቅ ለተጠቃሚዎች ስልጣን ያስጨብጣል፣
- ከኢንቨስትመንቱ እንደሚጠቀሙ ስለሚያውቁ ውሃን በሚቆጥብ ቴክኖሎጂ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ዋስትና ይሰጣል፣
- ለተጠቀሙበት ውሃ ክፍያ ቢጠየቁ በደስታ ለመክፈል ያበረታታቸዋል፣
- የውሃ ሃብቱን ከመበላሸት ይታደጋል፡፡

### የገጠር መሠረተ ልማት

ለመሠረተ ልማት የሚደረግ ኢንቨስትመንት አርሶ አደሮች ወደ ገበያ መር ግብርና እንዲያመሩ ጠንካራ ድርሻ አለው፡፡ በኤሽያ እንደሚታየው ልምድ የመሠረተ ልማት ትኩረት አጠቃላይ ትራንስፖርትን፣ ኮምኒኬሽንን፣ የገበያ መሠረተ ልማትን በማሻሻል በኩል ትኩረት ሲሰጥ፤ የግል ሴክተሩን ደግሞ በክምችትና በገበያ ፋሲሊቲዎች ላይ፣ በተለይ ሽቀጦች ሥራ ላይ መዋዕለ ንዋይ እንዲያፈሱ ማበረታታት ላይ ያተኩራል፡፡

በአንድ አካባቢ መንገድ ለመስራት ከዚያ አካባቢ የሚመረትን ምርትና ምርቱም ለገበያ የሚሆን መሆኑ እንደታሳቢ ይወሰዳል፡፡ የመሰረተ ልማት ፍላጎትን በቅደም ተከተል የማስቀመጡ ሂደትም ውስብስብ ነው፡፡ ምክንያቱም የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንት ለመተግበር ጊዜ ወሳጅ በመሆኑና የጥያቄውንም ቅደም ተከተል ለማስያዝ ጥንቃቄ የሚሻ ስለሚሆን ነው፡፡ በዋጋ ላይ ለሚደረግ ዋና ልውውጥ የኢንቨስትመንት ስትራቴጂ ማስተካከል ሲሰራ ከማክሮ ኢኮኖሚው የማስተካከል ዓላማ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም ይህ የኢንቨስትመንት ስትራቴጂ የግሉን ሴክተር መሪነት ያካተተ መሆን አለበት፡፡

**የድጋፍ አገልግሎት**

የገበያ መር የምርት ስርዓትንና ዳይቨርስፊኬሽንን ለማፋጠንና ለማመቻቸት ከሚኖር አጠቃላይ ፖሊሲ በተጨማሪ የድጋፍ አገልግሎት መኖር የሁለቱንም ጉዳዮች ጠቀሜታ ከመጨመር አልፎ በሂደቱ ሊመጣ የሚችለውን የተዛባ ውጤት ይቀንሳል፡፡ ከቀዳሚ የድጋፍ ፖሊሲዎች ውስጥም ጤናና ስርዓተ ምግብ ልዩ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ የስርዓተ ምግብ መሻሻል በጤናና በጥሩ አመጋገብ ላይ የተንጠለጠለ ነው፡፡ ከድሃ ቤተሰብና ማህበረሰብ ጤናና ንጽህና ጉድለት የሚመጣ የተዛባ ጤንነት ውጤት ከገበያ መር ምርት የሚገኘውን የገቢ እድገትና አወንታዊ ውጤት ሊጫነው ይችላል፡፡ ገቢና የምግብ ፍጆታ ማደግ ረሃብን ሊቀንስ ቢችልም ውስብስብ ካለው የምግብ እጥረትና የበሽታ ቁርኝት የሚነሳ የቅድመ ትምህርት ቤት የህጻናት የምግብ እጥረትን ሊያቃልል አይችልም፡፡ የማህበረሰቡን የጤና አገልግሎት ደረጃ በማሻሻል ጤናና ንጽህና በገጠሩ ውስጥ መስፋፋት አለበት፡፡ ይህም ስራ ከገበያ መር ምርት ስርዓት የሚገኘውን ጥሩ ውጤት ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም ያስችላል፡፡

# 6 ማጠቃለያ

ገበያ መር የግብርና ስርዓት በኢኮኖሚ እድገት የሚመጣና ዓለም አቀፋዊ የሆነ የማይቀር ክስተት ቢሆንም የዚህ ለውጥ ደረጃው ከሃገር ሃገርና ከአህጉር አህጉር ይለያያል፡፡ በዕርግጥ የለውጡ አቅጣጫ ግን በሁሉም ዘንድ ያው ገበያ መር ስርዓት መዘርጋት ነው፡፡ የመዋቅር ማስተካከልና የኢኮኖሚ ነጻነት ፖሊሲዎች በአሁኑ ሰዓት በማደግ ላይ ባሉ ሃገሮች በመተግበር ላይ ስለሆነ የገበያ መር ለውጥ ሂደቱን የበለጠ ያፋጥኑታል፡፡ ገበያ መር ሂደት የግብርና ፖሊሲ ማውጣትንና የምርምር አጀንዳን በቅደም ተከተል ማስቀመጥን ይጠይቃል፡፡ ይህም የፖሊሲ ለውጥ የምግብ ፍጆታን ለማርካት ተብሎ የተያዘ የምርት ስርዓት አሮጌ የምርት ስርዓት መሆኑን የመገንዘብ

ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪም ትርፍ ምርት በማምረት ላይ ከማተኮር ይልቅ የቤተሰቡን ገቢ ሊጨምር በሚችልና ከገበያ ጋር በተያያዘ  ስራ ላይ ማተኮር ይሆናል፡፡

በክልልም ሆነ በሃገር አቀፍ ደረጃ የምርት ምርጫ ሲባል በክልሉ ከሚታሰበው የምግብ ፍላጐት ላቅ ባለ አማራጭ ጠቀሜታ ይሆናል፡፡ የቤተሰብ ጉልበት አማራጭ ዋጋ መኖር የኮንትራት እርሻ እንዲለመድ ያደርጋል፡፡ ይሄውም በሙሉ እርሻውን ወይም ከእርሻ ሥራዎች ውስጥ የተወሰኑትን በመክፈል በኮንትራት ሊሰራ ይችላል ማለት ነው፡፡ ከግብርና ውጭ ባሉ የስራ መስኮች የመሰማራት እድልም ማደግ የሕይወት ማቆያ እርሻን መስፋፋት ይቀንሳል፡፡

ገበያ መር ምርት ሂደት ያለምንም እንከን ይጓዛል ብሎ ማሰብም አስቸጋሪ ነው፡፡ ቢያንስ ከአጭር እስከ መካከለኛ ባለ ጊዜ ሊደርስ የሚችል በገቢ እኩልነትና በአካባቢ ላይ የሚያስከትለው ሁኔታ ዝም ብሎ የሚታለፍ አይደለም፡፡ በተለይ ደግሞ ትክክለኛ ያልሆነ ፖሊሲ ካለ በተለይ ሰው ሰራሽ ግብዓትን ጥቅም ላይ በማዋል ከፍተኛ የአካባቢ ጤንነት ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ይህ ማለት አማራጭ የጉልበት ዋጋ መኖርና ክፍያውም መጨመር በእጅ ይታረም የነበረውን አረም በኬሚካል እንዲጠቀም ያስገድዳል፡፡ በመሠረቱ ለአትክልትና ፍራፍሬ ፀረ ተባይና ፀረ ፈንገስ መጠቀሙ ከልማዳዊው አሠራር በምርታማነት ላይ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በአግባቡ ጥቅም ላይ ካልዋለ ከፍተኛ የጤና ችግርና የአካባቢ ብክለት ያስከትላል፡፡ እንዲሁም የተፈጥሮ የሃብት መጠቀም መብት በአግባቡ ካልታየና ካልተያዘ የመሬትን ለምነት የማሳጣት ውጤትም ያስከትላል፡፡

ትክክለኛ የመንግስት ፖሊሲ በገበያ መር ሂደትና በዳይቨርስፊኬሽን መሸጋገሪያ ላይ ሊከሰት የሚችለውን አላስፈላጊ ውጤት ሊያስወግድ ይችላል፡፡ የገበያ መርን ሽግግር በሰከነ መንገድ ለማሸጋገር የሚያግዙ ነገሮች

- በገጠር ገበያ ላይ፣ በትራንስፖርት ላይ፣ በኮምኒኬሽን፣ በሰብል ማሻሻያ ምርምር ላይ፣ በኤክስቴንሽን ላይ፣ በአካባቢ ጥበቃ ላይ ኢንቨስት ማድረግ ወዘተ፣
- አርሶ አደሮች እንዲበረታቱና ምርታማነትን በሚጨምርና የተፈጥሮ ሃብትን በሚጠብቅ ቴክኖሎጂ ኢንቨስት እንዲያደርጉ የመሬትና የውሃ ዋስትና መብትን ማረጋገጥ፣
- ገበያ መር ሂደት ሲስፋፋ አደጋን ሊቀንስ የሚችል የካፒታል ገበያን ነጻ ማድረግ፣
- ገቢን ከገበያ መር ምርት ሂደት ወደ አጠቃላይ የሰው ልጅ ደህንነትን ጥቅም ሊያስፋፋ ወደ ሚችሉ እንደ ጤና፣ ንጽህና፣ ስርዓተ ምግብ የመሳሰሉ የአገልግሎት ድጋፎች አቅጣጫ መምራት ናቸው፡፡